# አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) በጤና መስክ ያከናወናቸው ተግባራት

## 1. የጤና ተቋማት ግንባታ

አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) የጤና ኬላዎችን እየገነባ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ማዋል የጀመረው በ1987 ዓ.ም. ነበር፡፡ በዚህ ዘመን የተገነቡት የጤና ኬላዎች ብዛት 3 ብቻ ሲሆን፤ ዛሬ በአልማ የተገነቡት የጤና ተቋሞች ብዛት 82 ደራሷል፡፡ ከዚህ ውስጥም 76 የጤና ኬላዎች(Health Center)፤ 3 ታዳጊ ጤና ጣቢያና (Cluster Health Center) 3 የእንስሳት ክሊኒክ (Animal Vet. Clinic) ናቸው፡፡










በአልማ የተገነባ የእንስሳት ጤና ኬላ (ሰሜን ወሎ፤ ጉባላፈቶ ወረዳ)

## 2. የህክምና መሣሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ማሟላት

- የሆስፒታል ቁሳቁስ ዕርዳታ (Medical equipments supply for hospitals) ብዛት 8
- የሽንት ቤት ግንባታ በባሕር ዳር ከተማ (Dry pit latrine in Bahir Dar Town) ብዛት 20
- የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት (Clean water supply for villages) ብዛት 7



ከአልማ ለጎንደር ሆስፒታል የተለገሰ ሆድ ሳይከፍት የኩላሊት ጠጠር ማውጫ መሣሪያ

## 3. የተዋልዶ ጤና አገልግሎት

አልማ ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ በክልላችን በሚገኙ በ10 ዞኖች 2,904 ወኪሎችን በማሠማራት ከ9 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ለሚሆን የህብረተሰብ ክፍል በጤናው ዘርፍ አገልግሎት በመሥጠት ላይ ይገኛል።

ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮም ይህንኑ አጠናክሮ በመቀጠል በክልላችን በሚገኙ 102 ወረዳዎች ውስጥ:-



ከአልማ ለባሕርዳር ሆስፒታል የተበረከቱ የህክምና መሣሪያዎች

- በቤተሰብ ምጣኔ (Family Planning)
- በእናቶችና ህፃናት ጤና እንክብካቤ (MCH)
- በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር በተለይም የፈቃደኛነት የደም ምርመራ(VCT)፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ በእርግዝና ጊዜ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ማድረግ(PMTCT) እና የዕድሜ ማራዘሚያ መድኃኒት እንዲያገኙ ማድረግ(ART)
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመከላከል እና
- በወጣቶች ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ህብረተሰቡን በማስተማር የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛል።



*አልማ ከገነባቸው የገጠር የንፁህ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክቶች አንዱ*

*መፀዳጃ ቤት (ባህር ዳር)*



## የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት

- በ9 ዓመታት ውስጥ 1,074,310 የሚሆኑ አዲስ ደንበኞችን አፍርቷል፡፡
- 2,437,151 የሚሆኑ ነባር ደንበኖች አሉት፡፡




የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ አርሶ አደር ሴቶች ጋር

## የእናቶችና ህፃናት ጤንነት ክብካቤ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፤ ደንበኞችን በጤና ተቋም ደረጃ ወደሚሰጥ አገልግሎት መላክ አንዱ የተዋልዶ ጤና ወኪሎች ተግባር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ደንበኞች ወደ ጤና ተቋም ከሚላኩባቸው አገልግሎቶች መካከል፦

### ሀ- የእናቶች ሪፈራል

እናቶች እንደ ለቅድመ ወሊድ፤ ለወሊድ፤ ለድህረ ወሊድ፤ ለቤተሰብ ዕቅድ፤ ለፊስቱላ ህክምና፤ ለክትባት፤ ለወሊድ መቆጣጠሪያ ተጓዳኝ ጠንቅ (Side effect) እና ለመሣሠሉት የተለያዩ አገልግሎቶች ይላካሉ፡፡ በ9 ዓመታት ውስጥም 656,878 እናቶችን ወደ ጤና ተቋማት ለመላክ ተችሏል፡፡

### ለ- የህፃናት ሪፈራል

የተዋልዶ ጤና ወኪሎች ህፃናትን ለተቅማጥ ህክምና፤ ለምግብ ዕጥረት መፍትሄ፤ ለክትባት እና ለመሣሠሉት አገልግሎቶች ይልካሉ፡፡ በ9 ዓመታት ውስጥ 1,487,892 ህፃናትን ወደ ጤና ተቋማት ለመላክ ተችሏል፡፡



## ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ

በወኪሎች ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ሥራ አንዱ ነው። ይህም በፈቃደኝነት ላይ ለተመሰረተ የደም ምርመራ፣ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለሚሰጥ ህክምና መላክን ያካትታል። በ9 ዓመታት ውስጥ የተከናወኑት ተግባራትም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

| የተሰጠ አገልግሎት | ክንውን |
|---|---|
| በፈቃደኝነት ላይ ለተመሰረተ የደም ምርመራ አገልግሎት | 147,373 |
| የኤድስ ህክምና | 3,160 |
| ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የሚሰጥ ህክምና | 13,902 |

## የወጣቶች ተዋልዶ ጤና

ወጣቱ ራሱን ከኤች አይ ቪ ኤድስና ሌሎች አባለዘር በሽታዎች እንዲከላከል እንዲሁም አምራችና ጤናማ ወጣት ለመፍጠር ማህበሩ ከተለያዩ ረጅ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የወጣቶች ተዋልዶ ጤና አገልግሎት እያካሄደ ይገኛል።

| ተ.ቁ. | ተግባራት | መለኪያ | ክንውን |
|---|---|---|---|
| 1 | ለወጣቶች ትምህርትና መረጃ ማዳረስ | | |
| | ክ/ጊዜ | በጊዜ | 1,410 |
| | አቻ ለአቻ ት/ት መስጠት | በቁጥር | 11,920 |
| | ክ/ጊዜ | በጊዜ | 775 |
| | አዝናንቶ ማስተማር | በቁጥር | 242,180 |
| | ወጣት ለወጣት ውይይት | በቁጥር | 39,310 |
| | ክ/ጊዜ | በጊዜ | 1,350 |
| | ቡና ጠጡ ፕሮግራም | በቁጥር | 38,810 |
| | የተሠራጩ የት/ት መርጃዎች | በቁጥር | 94,000 |
| 2 | ስልጠና መስጠት | | |
| | ለክበብ አመራር | በቁጥር | 725 |
| | የአቻ ለአቻ ስልጠና የአመቻች ስልጠና መስጠት | በቁጥር | 1,685 |
| 3 | በሪፈራልና ካውንስሊንግ ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶች | | |
| | የአቻ ለአቻ ምክር ለቤተሰብ | በቁጥር | 7,120 |
| | በፈቃደኛነት የተመሠረተ ምርመራ | በቁጥር | 11,540 |
| | የኮንደም ስርጭት | በቁጥር | 404,750 |